# የብሄር ብሄረሰቦች የመገንጠል መብት ዉስብስብነት

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

በሕገ መንግስቱ ካሉ አንቀጾች በሙሉ በብዛት የሚጠቀሰዉና የሚታወቀዉ አንቀጽ 39 ነዉ። በዚህ አንቀጽ ሕገ መንግስቱ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የመገንጠል መብት እንዳላቸዉ የሚደነግግ አንቀጽ ነዉ።

አንቀጽ 39 ስለ መገንጠል መብት ሲያወራ ከኢትዮጵያ የመገንጠሉን ሂደት እንጂ፣ አንድ ብሄር ብሄረሰብ ከአንድ ክልል ተለይቶ የራሱን ክልል ስለመመስረት አይደለም የሚናገረዉ። በአንድ ክልል የሚኖር ብሄር ብሄረሰብ የራሱን ክልል መመስረት የሚችልበትን ሁኔታ ሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 47 በግልጽ አስፍሮት እናያለን። ስለ አንቀጽ 47 እና በአጠቃላይ ስለ ክልሎች ፌደራል አወቃቀር ወደፊት በሰፊት የምንመለስበት ጉዳይ ይሆናል።

አንቀጹ 39 አምስት ንኡስ አንቀጾች አሉት። ንኡስ አንቀጽ 2 እና ንኡስ አንቀጽ 3 ከመገንጠል መብት ጋር ብዙም ግንኙነት ስለሌላቸዉ ስለነርሱ በዚህ ወቅት አናነሳም። በንኡስ አንቀጽ 5 ብሄር ብሄርሰብና ሕዝቦች ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አጠር ያለ ትርጓሜ እናገኛለን።

ንኡስ አንቀጽ 1 «ማንኛዉም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለዉ መብቱ በማናቸዉም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነዉ።» ይላል። «ያለ ገደብ፣ በማናቸዉም መልኩ» የሚሉት ቃላት ላይ ላተኮርባቸዉ እወዳለሁ።

በዚሁ አንቀጽ 39 ትንሽ ወረድ ብሎ በንኡስ አንቀጽ አራት «ያለ ገደብ እና በማናቸዉም መልኩ» የተባለዉ አባባል ሲሻር እናያለን። ብሄር ብሄረሰቦች መገንጠል መፈለጋቸዉ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ከመገንጠላቸዉ በፊት መሟላት ያለባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ ንኡስ አንቀጽ አራት ይተነትናል። ይህ አንዱ በሕገ መንግስቱ ያሉ እርስ በርሳቸዉ የሚቃረኑ ነጥቦች ናቸዉ።

በንኡስ አንቀጽ 4 ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ለመገንጠል ከፈለጉ መሟላት ያለባቸዉን የሚከተሉትን መስፈርቶች ያስቀምጣል፡

ሀ. የመገንጠል ጥያቄ በብሄር፣ ብሄረሰቡ ወይንም በሕዝቡ የሕግ አዉጭ ምክር ቤት በሁለት
ሶስተኛ ድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ
ለ. የፌደራሉ መንግስት የብሄር፣ የብሄረሰቡ ወይንም የሕዝቡ ምክር ቤት ዉሳኔ በደረሰዉ
በሶስት አመት ጊዜ ዉስጥ ለጠያቂዉ ብሄር፣ ብሄረሰብ ወይንም ሕዝብ ዉሳኔ ሲያደራጅ

ሐ. የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝቡ ዉሳኔዉ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ
መ. የፌደራሉ መንግስት መገንጠሉን ለመረጠዉ ብሄር፣ ብሄረሰብ ወይንም ሕዝብ ምክር ቤት
ስልጣኑን ሲያስረክብ
ሠ. በሕግ በሚወሰነዉ መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረገ ነዉ

በንኡስ አንቀጽ 5 «በዚህ ሕገ መንግስት ዉስጥ «ብሄር፣ ብሄረሰብና ሕዝብ» ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸዉን ባህርይ የሚያሳይ ማህበረሰብ ነዉ። ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይንም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸዉ፣ ሊግባቡት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸዉ፣ የጋራ ወይንም የተዛመደ ሕልዉና አለን ብለዉ የሚያምኑ፤ የስነ ልቦና አንድነት ያላቸዉና በአብዛኛዉ በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖሩ ናቸዉ» የሚለዉን ለብሄር ብሄረሰብና ሕዝቦች የተሰጠዉን ትርጓሜ እናነባለን።

አንዳንዶች ክልልን እንደ ብሄር ብሄረሰብና ሕዝብ፣ በስህተት የሚወስዱ ወገኖች አሉ። ነገር ግን በሕግ መንግስቱ መሰረት ብሄር ብሄረሰብ፣ ክልል ማለት እንዳልሆነ በግልጽ የሚያሳዩ ነጥቦች አሉ።

በአንቀጽ 46 «የፌደራሉ መንግስት በክልሎች የተዋቀረ ነዉ። ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ የማንነት እና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነዉ» ሲል ክልል ከፌደራል መንግስት ቀጥሎ ያለ የመንግስት አወቃቀር እንደሆነ ያስቀምጣል።

በአንድ ክልል ዉስጥ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች እንዳሉ የታወቀ ነዉ። በኢትዮጵያ ዘጠኝ ክልሎች ሲኖሩ ከሰማኒያ በላይ ብሄር ብሄረሰቦች አሉ። ለምሳሌ በደቡብ ክልል ከአምሳ በላይ ብሄር ብሄረሰቦች አሉ። በኦሮሚያ ክልል ጉራጌዎች፣ ሶማሌዎች፣ አማራዎች ፣ ከፊቾዎች ናቸዉ የሚባሉ በብዛት ይኖራሉ። በአማራዉ ክልል በወሎ በርካታ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች አሉ። በትግራይ ክልል ከጎንደርና ከወሎ የተወሰዱ ግዛቶች ወደ ትግራይ በመጠቃለላቸዉ «ትግሬ» አይደለንም የሚሉ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች የትግራይ ነዋሪዎች ተደርገዋል። ስለዚህ በምንም መስፈርትና ሚዛን ብሄር ብሄረሰብ ክልል ሊሆን እንደማይችል በግልጽ እናያለን።

አንቀጽ 47ን ብንመለከተ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸዉን ክልል ሲመሰርቱ መሟላት ያለባቸዉን መስፈርቶች እናገኛለን። በዚያ የክልል መንግስትና የብሄር ብሄረሰቦች ምክር ቤት የሚባሉት ተለይተዉ ነዉ የተጠቀሱት። አንድ እንዳልሆኑ በግልጽ ያሳያል።

ስለዚህ ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ብሄር ብሄረሰብ ማለት ክልል ማለት እንዳልሆነ ካረጋገጥን፣ በአንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የሰፈረዉ የመገንጠል መብት የተሰጠዉ፣ ለክልሎች ሳይሆን ለብሄር ብሄረሰቦች እንደሆነ ተደረጎ ነዉ ማስቀመጥ የሚቻለዉ። በሌላ አባባል የኦሮሚያ ክልል፣ የትግራይ ክልል፣ የሶማሌ ክልል በራሳቸዉ ሊገነጠሉ የሚችሉበት መንገድ የለም ማለት ነዉ። አንቀጽ 39 ክልሎችን የሚመለከት ስላልሆነ ...

የብሄር ብሄረሰቦች የመገንጠል መብት ተግባራዊ እንዲሆን ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል የመጀመሪያዉ «የመገንጠል ጥያቄዉ በብሄር፣ ብሄረሰቡ ወይንም በሕዝቡ የሕግ

አዉጭ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ነዉ» የሚል ነዉ።

እዚህ ላይ ሌላ ትልቅ መሰረታዊ ችግር አፍጦ ወጥቶ እናያለን ። ለምሳሌ የጉራጌ ብሄር ብሄረሰብና ሕዝብ መገንጠል ቢፈልግ የትኛዉ የጉራጌ ብሄር ብሄረሰብ ሕዝብ ምክር ቤት ነዉ በጉዳዩ ላይ ድምጽ የሚሰጠዉ ? በኢትዮጵያ ያለዉ የመንግስት መዋቅር ፌደራል፣ ከዚያም ክልል ብሎ ዞን ወረዳ እያለ የሚወርድ እንጂ የተለየ የጉራጌዎች ወይንም ኦሮሞዎች ወይንም ትግሬዎች ምክር ቤት ያለ አይመስለኝም። ይህም ሕገ መንግስቱ በብሄረ ብሄረሰቦች እስከ መገንጠል በሚለዉ ዙሪያ ያለዉ ትልቅ የተፋለሰ መሰረታዊ ችግር እንደሆነ እናያለን።

በሕገ መንግስቱ ብሄር ብሄረሰብ ማለት ክልል ማለት እንዳልሆነ አይተናል። ነገር ግን በአንቀጽ 39 የሕገ መንግስቱ አርቃቂዎች «ብሄር ብሄረሰቦች» ሲሉ ክልሎችን ማለታቸዉ እንደሆነ ተደርጎ በሕገ መንግስቱ ከተጻፈዉ ዉጭ አንዳንዶች ሊያስቡ ይችላሉ። እነዚህ ወገኖች የሚያስቡትን ትክክል አድርገን በመላ ምት ብንወስድ እንኳን፣ የብሄር ብሄረሰብን መብት በማስከበር ላይ አተኩሪያለሁ የሚለዉ ይህ ሕገ መንግስት ለሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እኩል መብት የማይሰጥ እንደሆነ ሊያመለክት ይችላል።

ለምሳሌ የየጁ ኦሮሞዎች መገንጠል ከፈለጉና «ባህር ዳር የሚቀመጠዉ የአማራዉ ክልል ምክር ቤት ነዉ ዉሳኔ የሚያሳልፍላቸዉ» ከተባለ ከጎንደር፣ ከሰሜን ሸዋ፣ ከጎጃም የመጡ የአማራዉ ክልል አማርኛ ተናጋሪ ተወካዮች የየጁዎችን ጥያቄ በቀላሉ ዉድቅ ማድረጋቸዉ አይቀርም። በናዝሬት በደብረ ዘይት በአዲስ አበባ ዙሪያ፣ በባሌ ጎባ፣ በመቱ እንዲሁም በበርካታ የኦሮሚያ ከተሞች የሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች ወይንም በወልቂጤና በወሊሶ የሚኖሩ ጉራጌዎች የመገንጠል ጥያቄ ቢያቀርቡ በኦሮምኛ ተናጋሪዎች ብቻ የተሞላዉ የኦሮሚያ ምክር ቤት ዉድቅ ማድረጉ አይቀርም። (በኦሮሚያ ምክር ቤት ኦሮምኛ የሚናገር ሰዉ ካልሆነ በስተቀር የመመረጥ መብት፣ በኦሮሚያ ክልል መንግስት መሥሪያ ቤት የመስራት መብት እንደሌለ ይታወቃል)

ታዲያ የየጁ ኦሮሞዎች፣ በወሊሶና ወልቂጤ ያሉ ጉራጌዎች፣ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች በብዛት የሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች፣ በአንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ ላይ ያለዉ ሕገ መንግስታዊ መብታቸዉ ተከበረላቸው ማለት ይቻላልን ? ወይስ በየጁ ያሉ ኦሮሞዎች ፣ በወልቂጤ ያሉ ጉራጌዎች፣ በናዝሬት ያሉ አማርኛ ተናጋሪዎች እንደ ብሄር ብሄረሰብ ተደርገዉ ሊቆጠሩ አይገባም ማለት ነዉን? እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ለአንድ ብሄር ብሄረሰብ የተሰጠ መብት ለሌሎች ተነፈገ ማለት አይደለምን?

ብሄር ብሄረሰቦች ከኢትዮጵያ የመገንጠል መብታቸዉ እንዲረጋገጥ መሟላት ያለበት ሁለተኛ መስፈርት «የፌደራሉ መንግስት የብሄር፣ የብሄረሰቡ ወይንም የሕዝቡ ምክር ቤት ዉሳኔ በደረሰዉ በሶስት አመት ጊዜ ዉስጥ ለጠያቂዉ ብሄር፣ ብሄረሰብ ወይንም ሕዝብ ዉሳኔ ሲያደራጅ ነዉ» የሚል ነዉ። ፌደራል መንግስቱ ከየትኛዉ ምክር ቤት ነዉ ጥሪ የሚቀርብለት ? እንዴት ነዉ ሕዝበ ዉሳኔ የሚያደራጀዉ ? ለነዚህ ጥያቄዎች ሕገ መንግስቱ መልስ አይሰጥም።

ሶስተኛዉ መስፈርት «የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝቡ ዉሳኔዉ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ነዉ» የሚል ነዉ። በማንም አገር ምርጫ ወይንም ሕዝብ ዉሳኔ ሲደረግ መራጩ ወይንም ድምጽ ሰጪዉ መታወቅ አለበት። አንድ ብሄር ብሄረሰብ ወይንም ሕዝብ፣ ሕዘብ ዉሳኔ እንዲሰጥ ከተፈለገ የዚህ ብሄር ብሄረሰብና ሕዝብ አባላት በግልጽ መታወቅ ይኖርባቿል። የዚህ ብሄር ብሄረሰብ አባል መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ሊኖረዉ ይገባል። ይህም በራሱ ትልቅ ችግርና ራስ ምታት የሚፈጥር እንደሆነ ብዙም አያከራክርም።

ለምሳሌ ኦሮሞ የሚባለዉን ብሄር ብሄርሰብና ህዝብ እንመልከት። ይህ የኦሮሞ ብሄር ብሄረሰብና ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄ ቢኖረዉ «ኦሮሞ» ተብሎ በሕዝበ ዉሳኔዉ ለመሳተፍ የትኛዉ ኢትዮጵያዊ ነዉ የምርጫ ወረቀት የሚሰጠዉ ? የመጀመሪያዉ ቋንቋ ኦሮምኛ የሆነዉ ነዉ ? ወይንስ እራሱን «ኦሮሞ» ብሎ የሚጠራዉ ? ወይንስ የአባት ዘር ነዉ የሚታየዉ ? ወይም በኦሮሚያ የተወለደ ሰዉ ነዉ ኦሮሞ የሚባለዉ ? ምንድን ነዉ የኦሮሞነት መመዘኛዉ? ማን ነዉ ኦሮሞ ? ኦሮሞ ነኝ ብሎ ኦሮምኛ የማይናገር ኦሮሞ ነዉን ? ኦሮምያ ዉስጥ ተወልዶ ኦሮምኛ የማይናገር ኦሮሞ ነዉን ? ኦሮሚያ ዉስጥ ተወልዶ ኦሮሞኛ የሚችል ነገር ግን ኦሮሞ አይደለሁም የሚል እርሱ ኦሮሞ ነዉን ? «አገሌ ኦሮሞ አይደለም፣ እገሌ ኦሮሞ ነዉ» የሚባል ዉዝግብ ቢነሳ ማን ነዉ ፈራጁ ?

አንድ የማዉቀዉ ሰዉ አለ። አንድ አያቱ የቦረና ሁለተኛ አያቱ የአዳ ኦሮሞዎች ናቸዉ። ሶስተኛ አያቱ የጂማ ኦሮሞና የሸንኮራ ቅልቅል ናቸዉ። አራተኛው አያቱ የደጀን ጎጃም ሰዉ ናቸው። አንደኛ ቋንቋዉ አማርኛ ነዉ። የተወለደዉና ያደገዉ አዳማ ናዝሬት ነዉ። ባለቤቱና የልጆቹ እናት፣ አባቷ የዉቁሮ ትግራይ ሰዉ ሲሆኑ እናቷ የአዲቋላ (ኤርትራ) ሴት ናቸዉ። ይህ ሰዉ «ኦሮሞ» ሊባል ይችላልን ? ሕዝብ ዉሳኔ ቢሰጥ ይህ ሰዉ የኦሮሞ ብሄር ብሄር ብሄረሰብ አባል ተደረጎ የምርጫ ካርድ ይሰጠዋልን ? ልጆቹስ ? ሚስቱስ በናዝሬት አዳማ እየኖረች በድምጸ ዉሳኔዉ መሳተፍ አትችልምን ? ሕገ መንግስቱ ለዚህ መልስ የለዉም።

ሌላዉ ትልቁ ችግር ደግሞ አንድ ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ በአንድ አካባቢ የሰፈረ ካለመሆኑ የተነሳ የሚፈጠረዉ ችግር ነዉ። ለምሳሌ «ማን ነዉ ኦሮሞ?» ለሚለዉ ጥያቄ «የመጀመሪያዉ ቋንቋ ኦሮምኛ የሆነ» ብለን እንዉሰድ። ኦሮምኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸዉ የሆኑ ሰዎች በኦሮሚያ ዉስጥ በብዛት ቢኖሩም፣ በአማራዉ ፣ በሶማሌ፣ በደቡብ፣ በበነሻንጉል ክልልችም በብዛት አሉ።

የኦሮሞ ብሄር ብሄረሰብ የመገንጠል ጥያቄ አቀረበ ቢባል ድምጽ የሚሰጡት በሁሉም ክልሎች ያሉ ኦሮሞ ናቸዉ የሚባሉት ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ናቸዉ ወይንስ በአንድ ክልል ብቻ ያሉ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች? በዚህ ጉዳይ የክልል መንግስታት ሚና ምንድን ነዉ ? ለዚህ ሁሉ ሕገ መንግስቱ መልስ አይሰጥም።

ሶስተኛዉ ችግር በአንድ ክልል ዉስጥ የሚኖሩ የአንድ ብሄር ብሄረሰብ አባላት የመገንጠል ጥያቄ ሲያቀርቡ የትኛዉን የክልል መሬት ይዘዉ ሊገነጠሉ እንደሚችሉ የተጠቀሰ ነገር አለመኖሩ ነዉ። በሕገ መንግስቱ ያለዉ የክልል ግዛቶች እንጂ፣ አንድ ብሄር ብሄረሰብን የሚከልል መልክአ መሬት አልተቀመጠም። ስለዚህ የተወሰነ መልክአ መሬት በሌለበት

የሚነሳ የመገንጠል ጥያቄ፣ ተግባራዊ ሊሆን የማይችል፣ ትርጉም የለሽ አሊያም ወደፊት ብጥብጥ ሊያመጣ የሚችል አሳሳቢና የተወሳሰበ ጉዳይ ነዉ።

አራተኛዉ መስፈርት «የፌደራሉ መንግስት መገንጠሉን ለመረጠዉ ብሄር፣ ብሄረሰብ ወይንም ሕዝብ ምክር ቤት ስልጣኑን ሲያስረክብ ነዉ» የሚል ነዉ። በዚህ መስፈርትም ከላይ እንደተብራሩት መስፈርቶች፣ አንድ ብሄር ብሄረሰብ ምክር ቤት በሌለበት የፌደራል መንግስቱ ስልጣኑን ለማን እንደሚያስረክብ አይታወቅም።

አምስተኛዉ መስፈርት በሕግ በሚወሰነዉ መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነዉ ይላል። ብሄር ብሄርሰቡ የሚኖርበት መልክዓ ምድርና ብሄር ብሄረሰቡን የሚወክሉት አካላት ማን እንደሆኑ ባልተወሰነበት ሁኔታ ለማን ነዉ ርክክብ የሚደረገዉ ? በብዙ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ ሕገ መንግስቱ፣ ፈረንጆች እንደሚሉት ቫኪዩም ወይንም ትለቅ ክፍተት ያለዉ ነዉ።

በጥቅሉ ስናየዉ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 4 እርስ በርሳቸዉ የሚቃረኑ፣ ክልልንና ብሄር ብሄረሰብ የሚያምታቱ፣ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ፣ እንደ ሕግ አንቀጽ መቀመጥ ያልነበረባቸዉ ንኡስ አንቀጾች ናቸዉ።

ሕገ መንግስቱ ከላይ ለዘረዘርኳቸዉ ቁልፍ ጉዳዮች ሕጋዊ ምላሽ የሚሰጥ ሰነድ አለመሆኑ፣ የሕገ መንግስቱ አርቃቂዎች የሕግ ባለሞያዎች እንዳልነበሩ፣ ከነበሩም ደግሞ የፖለቲካ ተጽእኖ እንደነበረባቸዉ በግልጽ የሚያሳይ ነዉ። በአንቀጽ 39 የሰፈሩት፣ መገንጠልን የሚደነግጉት ንኡስ አንቀጽ 1 እና 4 ፣ በሕግ እንዲሁም በሎጂክ ሚዛን ሲለኩ የተወሳሰቡና እርስ በርሳቸዉ የሚጋጩ፣ ትልቅ ችግር ያላባቸዉ ሆነው ነዉ ያገኘኋቸዉ።

በዚህም ምክንያት አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 4 ን ባላካተተ መልኩ መሻሻል አለበት እላለሁ። ሕገ መንግስት የሕግ ሰነድ እንጂ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደለም። በመሆኑም ሕገ መንግስቱ የሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝብ የሚወክል ሕገ መንግስት እንደመሆኑ፣ የሕግ ሰነዶች ሊኖራቸዉ የሚገባዉን ፕሮፌሽናል ጥራት ይዞ እንደገና መሻሻል አለበት እላለሁ። በዉስጡ ትርጉም የማይሰጡ እርስ በርሳቸዉ በጎላ መልኩ የሚቃረኑ ፣ እንዲሁ ለፖለቲካ ፍጆታ ተብለዉ የተሰገሰጉ አንቀጾች መዉጣት አለባቸዉ። እንደግ ፣ እንሻሻል እላለሁኝ።